# የኤችአይቪ ምርመራ ለእርስዎ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

## ለኤችአይቪ መመርመር ያለብኝ ለምንድ ነው?

- ኤችአይቪ ካለብዎት ሐኪምዎ ኤችአይቪ በሰውነትዎ የተፈጥሮ መከላከያ ላይ ምን ጉዳት እያደረሰ እንደሆነ ሊከታተሉ ይቻላሉ። ሐኪምዎ እርስዎ ጤናማ ሆነው እንዲቀዩ እና የሕክምና እርዳታን መቼ እንደሚጀምሩ ውሳኔ ለማድረግ ይረዱዎታል።
- እርጉዝ ከሆኑ ወይም እርጉዝ የሚሆኑ ከሆነ ለሕጻንዎ ኤችአይቪን ለማስተላለፍ ያለውን አደጋ ሊቀንሱ ይችላሉ።
- ኤችአይቪ እንዳለዎት ካወቁ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉቸው ሰው በበሽታው እንዳይለከፉ ሊከላከሉ ይችላሉ።
- ኤችአይቪ ካለዎት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረጉቸውን ሰዎች ወይም ሱስ የሚያሲዙ ዕፆችን የተጋሯቸው ሰዎች የኤችአይቪ ምርመራ እንዲያደርጉ መርዳት አስፈላጊ ነው። የምርመራ አማካሪው ልጆችዎም ምርመራ ያስፈልጋቸው እንደሆን ለመወሰን ሊረዱዎት ይችላሉ።
- አንዳንድ ጊዜ ያገቡ ባለትዳሮች ከትዳር ባለቤታቸው በተጨማሪ ከሌሎች ሰዎች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደርጋሉ። የትዳር ባለቤትዎ ከእርስዎ በተጨማሪ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊያደርጉ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ካሉ፡ እርግጠኛ ቢሆኑም ባይሆኑም የኤችአይቪ ምርመራ ማድረግ ይገባዎታል።
- የጥርስ ወይም የሌላ ሕክምና በሌላ ሃገር ውስጥ አድርገው ከሆነ የሌላ ሰው ደም የነካቸው የሕክምና መሣሪያዎች ለእርስዎ ሕክምና ከመዋላቸው በፊት ሳይጸዱ የቀሩ ሊሆኑ ይችላሉ።
- የኤችአይቪ ምርመራ የአእምሮ ሰላም ሊሰጠዎት ይችላል። ኤችአይቪ እንዳለዎት የሚያውቁበት እርግጠኛ መንገድ ምርመራ ማድረጉ ማድረግ ነው።

## ኤችአይቪ ምንድን ነው?

ኤችአይቪ ሰውነት የተፈጥሮ ከበሽታ መከላከያውን የሚያጠቃ ቫይረስ ነው። ኤችአይቪ የሰውነትዎን የተፈጥሮ ከበሽታ መከላከያዎችን ያጠቃል። ከጊዜ በኋላ ኤችአይቪ የሰውነት ከበሽታ መከላከል ኃይሉን ያዳክማል። ለወትሮው በጤናማ ሰው ላይ ሊኖሩ የማይችሉትን ብዙ በበሽታ መለከፍንና ካንሰር እንዲከሰት ኤችአይቪ ቀላል ያደርገዋል። ኤችአይቪ ለሕይወት አደገኛ የሆነ ነው።

## ኤችአይቪ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው እንዴት ነው?

ኤችአይቪ በብዙ መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል፡

- ኮንዶም ሳያደርጉ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ
- የጎጅ ዕፆችን መውሰጃ መርፌዎች በጋራ መጠቀም
- የሌላ ሰው ደም ወደ ሰውነት መቀዳት
- በቀዶ ጥገና
- ምላጮችን፤ የጥርስ ቡርሾችን፤ የንቀሳት መርፌዎችን ወይም ሌሎች ደም የነካቸው ነገሮችን በጋራ መጠቀም።
- አንድ እናት ኤችአይቪ ካለባቸው ወደ ልጃቸው ሊተላለፍ ይችላል፡ በውልደት ጊዜ ወይም ጡት በማጥባት።

## ኤድስ ምንድን ነው?

የሰውነት የተፈጥሮ ከመሽታ መከላከያ ድከመት በሽታ (ኤድስ) የኤችአይቪ መያዝ የመጨረሻ ደረጃ ነው። አንድ ሰው ኤድስ ካለበት ኤችአይቪ በሰውነቱ የተፈጥሮ ከበሽታ መከላከያ ላይ ጽኑ ጉዳት አድርሷል ማለት ነው።

## ኤችአይቪ ሊይዝዎት የማይችልበት፡

- እጅ በመጨበጥ
- በመተቃቀፍ
- በመሳም
- የምግብ መመገቢያ ዕቃዎች በጋራ በመጠቀም
- ኤችአይቪ ወይም ኤድስ ያለባቸው ሰዎች ከነኳቸው ምግቦች ወይም ሌሎች ነገሮች
- ከመጸዳጃ መቀመጫ
- ከወባ ትንኝ ነክሻ

*ኤችአይቪ ኖሮዎት ግን ምንም የበሽታ ምልክት ሳይኖር ለብዙ ዓመታት ሊቆዩ ይችላሉ።*

## ከኤችአይቪ መከላከል የሚቻለው እንዴት ነው?

ከእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ የእርስዎን ሁኔታ የሚመለከቱትን ሊመርጡ ይችላሉ።

- ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ድርጊቶች መቆጠብ
- በፊንጢጣ ወይም በተለምዶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉ ከሆነ የላቴክስ ወይም የፖሊዩሪቴይን ኮንዶም ይጠቀሙ። ይህ ከኤችአይቪ፡ ከሔፕታይተስ ቢ እና ከሌሎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች እንዲጠበቁ ይረዳል።
- ኤችአይቪ ከሌለባቸው ሰውና ከእርስዎ ጋር ብቻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚያደርጉ አንድ ሰው ብቻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያድርጉ። የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉቸው ሰው ኤችአይቪ ካለባቸው ሁል ጊዜ ኮንዶም ይጠቀሙ።
- እርጉዝ የሆኑና ኤችአይቪ ያለዎት ከሆኑ ሕጻንዎን ከቫይረሱ ለመጠበቅ የሚረዳ መድሐኒት አለ።
- ሱስ የሚያሲዙ ዕጾች መውጊያ መርፌዎችን በፍጹም በጋራ አይጠቀሙ።

## የኤችአይቪ ምርምራ ካደረግሁኝ በኋላ መጠበቅ የምችለው ምንድን ነው?

ሐኪምዎ ወይም የኤችአይቪ ምርመራ አማካሪዎ ስለምርመራውና ከምርመራው በኋላ ምን እንደሚሆን ያወያዩዎታል። ለምርመራው ደምዎን ይወስዳሉ። አንዳንድ ጊዜ የምርመራውን ውጤት በዛኑ ቀን ሊያውቁ ይችላሉ። ግን ለወትሮው ከ 7 እስከ 10 ቀናት ይወስዳል። የምርመራውን ውጤት ለማወቅ ወደ ክልኒኩ ተመልሰው መሄድ ሊያስፈልግዎት ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች ከኤችአይቪ እና ከኤድስ ጉዳይ ጋር ስለሚገናኙ አሳፋሪ ነገሮች ያሳስባቸዋል። ለኤችአይቪ ምርመራ ማድረጋቸውን ወይም የኤችአይቪ ያለባቸው መሆናቸውን ሌሎች ሰዎች ያውቃሉ ብለው ይጨነቃሉ። ይህ የሚያስጨንቅዎት ከሆነ ሐኪምዎን ወይም የምርመራ አማካሪዎን እንዴት የግል ጉዳይዎ በሚስጥር ሊጠበቅ እንደሚችል ይጠይቁ። ምርመራዎና የምርመራው ውጤት በሚስጥር ተቀማጭ ይሆናል። እርስዎና ሐኪምዎ ወይም የምርመራ አማካሪዎ ብቻ ውጤቱን ታውቃላችሁ። ስለ ምርመራው ውጤት ከሐኪምዎ ወይም ከምርመራ አማካሪዎ ጋር የሌለብዎት ወይም ያለብዎቸ ስለመሆኑ ለመወያየት ይችላሉ።  ደግሞም ሊያስፈልግዎት ስለሚችል ማነኛውም እርዳታና ድጋፍ ይረዱዎታል።

## የምርመራ ውጤቴ በሽታው እንዳለብኝ የሚያመለክቸ ከሆነስ?

የምርመራ ውጤትዎ በሽታው እንዳለብዎት የሚያመለክቸ ከሆነ ኤችአይቪ አለብዎት ማለት ነው። ጤናማ ሆኖ ለመቆየትና ረጅም ጊዜ ለመኖር ማድረግ የሚችሏቸው ብዙ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው እርምጃ ኤችአይቪ ወይም ኤድስ የያዛቸውን ሰዎች በማከም ልምድ ያላቸውን ሐኪም መጎብኘት ነው። እኚህ ሐኪም ስለ ጤናዎ ምርመራ ያደርጉና ለኤችአይቪ ሕክምና ለማድረግ ስለሚኖሩት መድሐኒቶች እንዲያውቁ ይረዱዎታል።

ለኤችአይቪ ምንም መዳኛ ባይኖርም አዲስ መድሐኒቶች ኤችአይቪ ወይም ኤድስ ያለባቸውን ሰዎች ጤናንና የኑሮን ሁኔታዎችን በከፍተኛው አሻሽለውታል።

## የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረግኋቸው ሰዎችስ?

የኤችአይቪ ምርመራው የእርስዎን ብቻ ይመረምራል። ስለ ሚስትዎ፣ ባልዎ፣ የወንድ ፍቅረኛዎ፣ የሴት ፍቅረኛዎ ወይም ሌላ ሰው ሊያሳውቅዎት አይችልም። እነኚህ ሰዎች ኤችአይቪ እንዳለባቸው ለእራሳቸው የኤችአይቪ ምርመራ በማድረግ ብቻ ሊያውቁ

በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ የሕክምና ወጪዎችን ለመሸፈን የሚረዱ ብዙ ፕሮግራሞች አሉ ። ኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ ላለባቸው ሰዎች የነጻና የአነስተኛ ወጪ ጤና ጥበቃ በተጨማሪ ማወቅ ከፈለጉ፣ ሐኪምዎን ያማክሩ ወይም ለሚከተለው ይደውሉ፣

### *ኤች አይ ቪ/ኤስ ቲ ዲ ፕሮግራም*

ብቁ ለመሆን መሆን ያለበት፣
- ኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ ካለብዎት
- በዋሽንግተን ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ
- ገቢዎ አነስተኛ መሆን

ለተጨማሪ መረጃ፣ በ (206) 296-4649 ይደውሉ

## የኤችአይቪ ምርመራ ማድረግ የምችለው የት ነው?

ምርመራው በሚስጥር ተቀማጭ (እርስዎና ክልኒኩ ብቻ ስለምርመራው ታውቃላችሁ) ወይም ባልታወቀ ሰው ስም ሊሆን ይችላል (ስምዎን ላለመጠቀም ምርጫ ሊያደርጉ ይችላሉ)።
**(206) 296-4649 ይደውሉ**

የሐርበር ቪው የሕክምና ማዕከል የሕዝብ ጤና ኤስቲዲ (በግብረ ሥጋ ተላላፊ በሽታ) ክልኒክ በሚስጥርና ባልታወቀ ሰው ስም የሚቀመጥ በገቢ መጠን ሒሳብ በማስከፈል የኤችአይቪ ምርመራ ያደርጋል።

ያለቀጠሮ ስለመጎብኘት ወይም ቀጠሮ ስለመያዝ ለማወቅ (206) 744-3590 ይደውሉ። የቃል አስተርጓሚ ካስፈልገዎት ከቀ-ጠሮው በፊት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ክልኒኩ እንዲያውቅ ያድርጉ።

የኤችአይቪ ምርመራ ከሐኪምዎ ወይም ከጤና ክልኒክዎ ማግኘት ይችላሉ። ወጪው ይለያያል።

**ስለ ኤች አይ ቪ ወይም ኤች አይ ቪ ምርመራ በ ሚከተለው ይደውሉ፣**
**ኤች አይ ቪ/ኤስ ቲ ዲ ፕሮግራም**
**(206) 296-4649**

**www.kingcounty.gov/health/hiv**

Public Health
Seattle & King County

በተለየ መልክ ሊቀርብ ይችላል።

Revised July 2011 - Amharic